ሐዋላ ሌላ የብድር ውል ሌላ

በ ጌታሁን ወርቁ

የሰበር ችሎት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበትን ፍርድ የሚመለከት ችሎት ነው። ዋና ዓላማው ለተከራካሪዎች ፍትሕ ከመስጠት ባለፈ የሕግ ሥርዓቱን ወጥነት፣ ህልውናና ፍትሕ ማረጋገጥ ነው።

የኢትዮጵያ ፌዴራል ሕገ መንግሥት በአንቀጽ **80(3)** የፌዴራል ሰበር ችሎትን ያቋቋመ ሲሆን፣ ‹‹የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን ይኖረዋል፤›› በማለት ደንግጓል። ዝርዝሩ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር **25/1988** ዓ.ም. የወጣ ሲሆን፣ የአዋጁ አንቀጽ **10** የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥልጣንን ይዘረዝራል። በዚሁ መሠረት ሰበር ችሎቱ ሦስት የሥረ ነገር ሥልጣን ተሰጥቶታል። እነዚህም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠባቸው ጉዳዮች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች እንዲሁም የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት ወይም በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞባቸው ከተገኘ የፌዴራል ሰበር ችሎት ያርማቸዋል። የሰበር ጥያቄው ማመልከቻ የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠ በዘጠና ቀን ውስጥ ነው። በዚህ አዋጅ መሠረት የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ብዙ ጉዳዮችን የተመለከተ ሲሆን፣ ከሰኔ **1997** ዓ.ም. ጀምሮ ደግሞ የሰበር ችሎቱ ፍርድ በሥር ፍርድ ቤቶች አስገዳጅ እንዲሆን የሚያስችል አዋጅ ወጥቷል። አዋጅ ቁጥር **454/1997** ዓ.ም. በአንቀጽ **2** ‹‹የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሰጠው የሕግ ትርጉም በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል። ሆኖም የሰበር ችሎቱ በሌላ ጊዜ በተመሳሳይ ጭብጥ የተለየ ትርጉም ሊሰጥ ይችላል፤›› በማለት ደንግጓል። ይህ የሰበር ችሎቱ ሥልጣን በዳኛ ሠራሽ ሕግ ሥርዓት **(Common law countries)** ካለው የገዥ ፍርድ **/Precedent/** ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሥልጣን ቢሆንም፣ ችሎቱ ሕግ የማውጣት ሥልጣን የሌለው በመሆኑና ሥልጣኑም ከሰበር ችሎት ውጭ ለሌሎች ፍርድ ቤቶች ያልተሰጠ በመሆኑ ልዩነት አለው። በአዋጁ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሰጠባቸውን ውሳኔዎች በየደረጃው ላሉ ፍርድ ቤቶችና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት አሳትሞ የማሰራጨት ግዴታ ተጥሎበታል። በዚህ መሠረት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እስካሁን በ **14** ቅጾች **(Volumes)** የተካተቱ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሰጠባቸው ፍርዶች ያሳተመ ሲሆን፣ **15** ኛው በቅርብ ቀን እንደሚወጣ ይጠበቃል። እስካሁን በዚህ አምድ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጣቸው በርከት ያሉ ፍርዶች ላይ ትችት ያቀረብን ሲሆን፣ በዚህ ጽሑፍም ችሎቱ በሰጠው ፍርድ ላይ አጭር ምልከታ ለማድረግ ታስቧል። ጉዳዩ የሰበር ችሎቱ ከብድር ውል ማስረጃ ጋር በተያያዘ የሰጠውን ፍርድ የተመለከተ ሲሆን፣ ለጽሑፉ መነሻ የሆነውን ጉዳይ በመግለጽ ችሎቱ የሰጠውን ፍርድ ፍትኃዊነት ለመመልከት ይሞከራል።

መነሻ ጉዳይ

ጉዳዩ በሰበር መዝገብ ቁጥር **31737** የካቲት **27** ቀን **2000** ዓ.ም. ሰበር ችሎቱ በሰጠው ፍርድ የመጨረሻ እልባት አግኝቷል። በዚህ ጉዳይ አመልካችና ተጠሪ የሆኑት ግለሰቦች ሲሆኑ ጉዳዩ የብድር ውል ለማስረዳት ስለሚቀርብ ማስረጃ የተመለከተ ነው። አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ከተጠሪ ጋር በነበራቸው የንግድ ግንኙነት ተጠሪ ብር **50,000** እንዲያበድራቸው በስልክ ጠይቀዋቸው በሐዋላ የላኩላቸው መሆኑን ገልጸው ገንዘቡን ስላልመለሰ እንዲመልሱ ክስ አቅርበዋል። ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት በሰጡት መልስ የተባለውን ገንዘብ መቀበሌን አልክድም፣ ነገር ግን ገንዘቡን ከአመልካች ላይ የወሰድኩት ብድር ጠይቄ ሳይሆን አመልካች ከአሁን በፊት ከእኔ በብድር የወሰዱትን ገንዘብ ለመመለስ ልከውልኝ ነው፣ የገንዘብ መላኪያ ወረቀቱም በምንም ዓይነት የብድር ማስረጃ ሊሆን አይችልም፣ ከብር **500 (**አምስት መቶ**)** በላይ በሆነ ገንዘብ የተደረገ የብድር ውል በጽሑፍ ካልተደገፈ ዋጋ አይኖረውም በማለት ተከራክረዋል።

የመቀሌ ዙን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ በመጀመሪያ የማስረዳት ሸክሙ የሚወድቀው በማን ላይ ነው**?** የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ግራ ቀኙ ግንኙነታቸው በንግድ ላይ የተመሠረተ መሆኑን አልተካካዱም፣ የአሁን ተጠሪ ገንዘቡን መቀበላቸውን አልካዱም፣ አመልካች ተጠሪ ገንዘቡን የላኩት ቀደም ሲል ለነበረባቸው ዕዳ መክፈያ መሆኑን የማስረዳት የመጀመሪያ ግዴታ የሚወድቀው ተጠሪ ላይ ነው፣ ይህን እንጂ ተጠሪ ይህንኑ ለማረጋገጥ የሚያስችል የማስረጃ ዝርዝር ከመልሳቸው ጋር አላቀረቡም፣ በማስረጃ ያልተደገፈ የፍሬ ነገር ክርክር ደግሞ ዋጋ የሚሰጠው አይሆንም ካለ በኋላ ተጠሪ ገንዘቡን ከአመልካች መቀበላቸውን አምነው አመልካች ገንዘቡን የሰጧቸው በፊት ለነበረ ዕዳ መክፈያ መሆኑን አስካላረጋገጡ ድረስ ባለዕዳ ናቸው፣ በመሆኑም ተጠሪ ክሱ የቀረበበትን ብር **50,000 /**ሃምሳ ሺሕ/ ክሱ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ የባንክ ወለድ ጋር ለከሳሽ ይክፈሉ በማለት ወሰነ።

ተጠሪ ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ይግባኝ ተቀባይነት ባለማግኘቱ አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ችሎት አቅርበዋል። ሰበር ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር አዳምጦ በማስረጃነት የቀረበው የሐዋላ ወረቀት (ደረሰኝ) በግራ ቀኙ መካከል የብድር ውል መኖሩን የሚያረጋጋጥ ማስረጃ አይደለም የሐዋላ ወረቀት ገንዘብ ከአንድ ባንክ ወደ ሌላው የተላከ መሆኑን ከማረጋገጥ ውጪ በሌላ ተጨማሪ ማስረጃ ካልተደገፈ በቀር ገንዘቡ የተላከው በብድር መሆኑን አያስረዳም፣ ተጠሪ ገንዘቡ የተላከልኝ አመልካች ለነበረባቸው ዕዳ መክፈያ እንዲሆን ነው በማለት መመለሳቸውም ቢሆን ብድሩን አምነዋል የሚያስብላቸው አይደለም፣ በመሆኑም አመልካች ገንዘቡን የላኩት በብድር መሆኑን ተጠሪ አላመኑም ክህደት ካለ ደግሞ ብድሩ መኖሩን የማረጋገጥ (የማስረዳት) ኃላፊነቱ የአሁን አመልካች ነው፣ ስለዚህ የብድር ውል መኖሩ በአመልካች ሳይረጋገጥ ወይም በተጠሪ ሳይታመን የቀድሞው ብድር መኖሩን ተጠሪ የማስረዳት ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ ተጠሪ በክሱ የተጠየቀውን ገንዘብ እንዲከፍሉ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሯል በማለት ወስኗል።

አመልካች ጉዳዩን ለፌዴራል ሰበር ያቀረቡ ሲሆን ሰበር ችሎቱ በአብላጫ ድምፅ በሰጠው ፍርድ አመልካች ለተጠሪ የሰጡትን ብድር በሐዋላ ወረቀቱ በጽሑፍ በማረጋገጣቸውና ተጠሪም ገንዘቡን መቀበላቸውን በማመናቸው ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን በመግለጽ ተጠሪ ከአመልካች ጋር አለኝ የሚሉትን የብድር ውል በማስረጃ ባለማስረዳታቸው ተቃውሟቸው ውድቅ መሆኑን በገዥ ፍርዱ በማተት በከፍተኛ ፍርድ የቀረበባቸውን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፍሉ ፈርዶባቸዋል። ሰበር ችሎቱ በፍርዱ እንዳሰፈረው ‹‹ከፍ ብሎ በተጠቀሰው የሕግ አንቀጽ (2472) የብድር ውልን በጽሑፍ ማስረዳት እንደሚቻል በተደነገገው መሠረት ገንዘቡን የላኩበትን የሐዋላ ወረቀት በማቅረብ አረጋግጠው ያስረዱ ስለሆነ በከሳቸው ላይ ያቀረቡትን ፍሬ ነገር የማስረዳት ኃላፊነታቸውን ተወጥተዋል።›› በፍርዱ የልዩነት ሐሳብ ያላቸው ዳኛ በበኩላቸው «ከሳሽ በአስረጂነት ያቀረቡት ሰነድ በባንክ አማካይነት በሐዋላ ከአዲስ አበባ ወደ መቀሌ ለተከሳሽ ብር 50 ሺሕ መላካቸውን የሚያረጋግጥ ሰነድ ነው። የሐዋላ ሰነዱ በመካከላቸው የብድር ግንኙነት መኖሩን የማያረጋግጥ ከመሆኑም በላይ ተከሳሽም በባንክ በኩል የተላከውን ገንዘብ መቀበላቸውን ቢያምኑም ነገር ግን ገንዘቡን ከተከሳሽ የተቀባበሉት ከሳሽ እንደሚሉት ከራሳቸው በመበደራቸው ምክንያት ሳይሆን ቀደም ሲል ለከሳሽ አበድረውት ለነበረ ገንዘብ በመክፈያነት እንደተቀበሉ ገልጸው ብድሩን ክደው ተከራክረዋል፤» የሚል ትንተና በመስጠት የሥር ተጠሪ ላይ መወሰኑ ተገቢ አለመሆኑን ገልጸው የልዩነት ሐሳባቸውን አስፍረዋል።

የብድር ውልና ሊከተለው የሚገባው ፎርም

በኢትዮጵያ ሕግ ብድር ከውል የሚመነጭ ግዴታ ነው። በሕጉ የብድር ውል (የሚያልቅ ነገር ብድር ውል) ማለት ከተዋዋዮቹ አንዱ ወገን አበዳሪው ሌላውን ተበዳሪ ሰው የተበደረውን ነገር በዓይነቱ ለመመለስ ተገዳጅ በማድረግ ገንዘብ ወይም በማገልገል የሚያልቅ ሌላ ነገር ለተበዳሪው ለመስጠትና ሀብትነቱን ለማስተላለፍ የሚገደድበት ውል ነው። የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 2471 በመሆኑም ብድር በውል ላይ የሚመሠረት ግዴታ ሲሆን ተዋዋይ ወገኖችም የንፅፅር ግዴታ አንዱ ለሌላው የሚገባበት /For Consideration/ የሚደረግ ነው። በዚህ ረገድ በኢትዮጵያ ሕግ ዕውቅና የተሰጣቸው የተለያዩ የብድር ዓይነቶች አሉ። ከእነዚህ ውስጥ ለተለያዩ ዓላማዎች የሚሰጡ በተወሰነ ጊዜ የሚከፈሉ ብድሮች፣ ክፍት ብድር፣ ሌተር ኦፍ ክሬዲት ይገኙበታል።

እነዚህ ሁሉም ዓይነት ብድሮች በባንኮች የሚሰጡ ሲሆን፣ የተወሰኑት ደግሞ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የሚሰጡ ናቸው። በጎብረተሰባችን የተለመደውና በግለሰቦች መካከል በየዕለቱ ሲፈጸም የምናስተውለው በተወሰነ ጊዜ የሚመለስ ብድር ውል ነው። ሰበር ሰሚ ችሎት በወሰነውም በዚህ መዝገብ አከራካሪ ሆኖ የፍርድ ቤት ዳኝነት የተጠየቀበት ተመሳሳይ ውል ነው። አንድ ሰው የተወሰነ ገንዘብ ለሌላው በብድር መልክ ለመስጠት የተበደረውም ሰው በተወሰነ ጊዜ ገንዘቡን ከወለድ ጋር ወይም ያለ ወለድ ለመመለስ መስማማታቸው የተለመደ ሃቅ ነው። የገንዘቡ መጠንና የሚከተለው ፎርም ይለያይ እንጂ በቀን የብድር ውል ሳይፈጽም የሚቀር ሰው የለም እስኪባል ድረስ የብድር ውል የተለመደ ጎብረተሰባዊ ሁኔታ ነው።

የውል ፎርም (አቀራረፅ) በሕጋችን ከችሎታ፣ ከፈቃድና ከውለታ ጉዳይ በተሻለ ለተዋዋይ ወገኖች ነፃነት የተተወ ነው። ‹‹በሁለቱ ወገን ተዋዋዮች በማናቸውም ሁኔታ የተደረገ ስምምነት ውል ለማድረግ በቂ ነው፤›› በማለት ሕጉ ይህን ነፃነት ደንግጓል። የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1719/1/ በሌላ በኩል የውሉ አጻጻፍ ፎርም ወይም ዓይነት በሕግ የታዘዘ ሆኖ እንደ ትዕዛዙ ባይፈጸም ፈራሽነትን የሚያስከትል ይሆናል። የብድር ውልን በተመለከተ ግን በግልጽ የተቀመጠ የፎርም ግዴታ ባለመኖሩ ተዋዋይ ወገኖች በመሰላቸው መልኩ ሊያደርጉት ይችላሉ። ‹‹ሰነድ አሲዞ ገንዘብ መበደር›› ሲሆን በንግድ ሕጉ የብድር ውሉ በጽሑፍ መሆን አለበት ሲል በቁጥር 948 ደንግጓል። ውሉ በጽሑፍ ካልተደረገ ፍፁም ፈራሽ እንደሚሆን ስለሚገልጽ ይህ ድንጋጌ ለብድር ውል ፎርም ልዩ ሁኔታ /Exception/ ነው። ስለዚህ የብድር ውል በቃል፣ በድርጊት፣ ወይም በጽሑፍ ሊፈጸም ይችላል። በዚህ ረገድ ፎርም ለብድር ውል የሚያስፈልገው የውሉን ፍሬ ነገር

ለማስረዳት **/Ad-probationum/** እንጂ የውሉን ብቃት ለማሳየት **/Ad-validitatum/** አይደለም። ፎርሙ ባይጠበቅም በሌላ የማስረዳት ዘዴ የውሉን መኖር ማሳየት ይችላሉ። የብድር ውል በጽሑፍ መደረጉ የውሉን ነገር ለማስረዳት ጠቃሚ መሆኑ አያጠያይቅም። ስለ ብድር የደነገገው የፍትሐ ብሔር ሕጋችን የብድር ውልን ለማስረዳት የተለያዩ ማስረጃዎች ያስቀመጠ ሲሆን ባንኮችን በተመለከተ ልዩ ጥበቃ ያደርጋል። በብድር የተሰጠው ገንዘብ ከብር **500** በላይ ሲሆን፣ የብድሩን ውል በጽሑፍ ወይም በፍርድ ቤት በተደረገ የእምነት ቃል ወይም መሐላ ካልሆነ በቀር ለማስረዳት አይቻልም። የብድር መከፈል ማስረጃም በተመሳሳይ መልኩ ይፈጸማል። ሆኖም ይህ የማስረጃ ዓይነት በባንኮችና በደንበኞቻቸው መካከል ያለውን ግንኙነት አይመለከትም። ከባንኮች ጋር የሚፈረም የብድርን ውል ወይም የተበዳሪውን ገንዘብ መልሶ መክፈልን በምስክሮች ወይም በአዕምሮ ግምት ማስረጃ ማስረዳት ይቻላል። የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር **2473/2/** በመሆኑም ሕጉ ባንኮችን በተመለከተ ቀለል ያለ የማስረጃ ዓይነት ደንግጓል።

ተዋዋይ ወገኖች የብድር ውላቸው በጽሑፍ እንዲደረግ ወስነውና በውሉ ይዘት በምስክር መረጋገጥ እንዲገባው ከተስማሙ በሁለት ምስክሮች አለመረጋገጡ ውሉን ፈራሽ ያደርገዋል። የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር **1727** ተዋዋዮቹ ለሚዋዋሉት ውል ሕግ የሚያስገድደውን ልዩ አኳኋን **(ፎርም)** ለመፈጸም የተስማሙ እንደሆነ ለምሳሌ ሕግ ሳያስገድድ በጽሑፍ ለመዋዋል የተስማሙ ሲሆን፣ ውሉ ፍፁም የሚሆነው የተስማሙበትን የውላቸውን አፈጻጸም ሞልተው በተዋዋሉ ጊዜ ብቻ ነው በሚል ይደነግጋል። ተዋዋይ ወገኖች በውሉ ላይ መፈረም የሚገባቸው በተመሳሳይ መልኩ ይህ በውሉ ላይ ሰፍሮ ሲገኝ ብቻ ነው። የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከኪራይ ውል ጋር በተያያዘ በመዝገብ ቁጥር **15992** ሐምሌ **19** ቀን **1997** ዓ.ም. በሰጠው ገዥ ውሳኔ **/Precedent/** ተመሳሳይ አቋም ይዟል። ሰበር ሰሚ ችሎቱ በገዥ ፍርዱ እንዳሰፈረው፦

‹‹... በቁጥር **1719** እንደተገለጸው በመርህ ደረጃ ውል ለመዋዋል የስምምነት መኖር ብቻ በቂ በመሆኑ ውሉን እንዲፀና ተዋዋዮች እንዲፈጸም የፈለጉት ተጨማሪ ፎርማሊቲ ምን እንደሆነ ማወቅ የሚቻለው ተዋዋዮቹ ባደረጉት ውል ብቻ ነው። ስለዚህ የፎርሙን ዓይነት፣ የምስክሮቹን ብዛት፣ የመመዝገብ አስፈላጊነት፣ አዋዋይ ፊት ስለመቅረብ ወዘተ. ተዋዋዮቹ በፍላጎት የጨመሩት ፎርም ስለመኖሩ በተዋዋዮቹ መካከል ከተደረገው ስምምነት መገንዘብ መቻል አለበት። ተዋዋዮቹ ውላቸውን በጽሑፍ ካሰፈሩ የጹሑፉን ፎርማሊቲ እንደፈለጉ መገመት ቢቻልም፣ ይህ በጽሑፍ የሰፈረው ስምምነት በምስክሮች እንዲረጋገጥ ወይም እንዲመዘገብ ወይም አዋዋይ ፊት እንዲቀርብ መፈለጋቸውን የሚያሳይ አይሆንም። በጽሑፍ ከመሆኑ በተጨማሪ ሌሎቹንም ፎርማሊቲዎች እንዲያሟሉ መፈለጋቸውን በጽሑፉ በራሱ ወይም በሌላ መልክ ስምምነት መኖሩን የሚያሳይ ነገር መኖር አለበት።››

ከዚህ አንፃር ለምሳሌ ባንኮች የብድር ውልን በጽሑፍ ከማድረግ በተጨማሪ በምስክሮች እንዲረጋገጥ ማድረጉ ችግር ባይኖረውም በሕግ የተቀመጠ ግዴታ አይደለም። የባንኮች የብድር ውል በምስክሮች ባይረጋገጥም እንኳን በሕግ ፊት ተቀባይነት ይኖረዋል። ተዋዋይ ወገኖች የፈረሙት ሰነድ በመካከላቸው የውል ግንኙነት ለመመሥረት በቂና ብቸኛ ፎርም አድርገው ከተቀበሉት ፍርድ ቤቶች ፍላጎታቸውን ከማስፈጸም ሌላ ተጨማሪ ፎርም ሊጠይቁ አይገባም።

ፊርማና ምስክሮች ጋር በተያያዘ ግን ሕጉ ያስቀመጠውን ድንጋጌ ልብ ማለት ያስፈልጋል። ፊርማ በውሉ ተገዳጅ በሆነው ሰው እጅ መጻፍ ይገባዋል። ለመፈረም የማይችል ሰው በጽሕፈት ፊርማው ፋንታ የጣት ምልክት መተካት ይችላል። ማየት የተሳናቸው ወይም የመሐይምናን ፊርማ የጣት ምልክት ፊርማ የነሱ ፊርማ መሆኑን ውል አዋዋይ ሹም ወይም አንድ ፍርድ ፀሐፊ ወይም አንድ ዳኛ በሥራቸው ላይ ያረጋገጧቸው ካልሆነ አያስገድዳቸውም። ከእነዚህ ሁኔታዎች ጋር ተያይዞ የሚነሱ ነጥቦች አሉ። ለምሳሌ ነጋዴ ባለሙያ ስለሆነ ‹‹መሐይምናን›› ከሚባሉ ወገኖች ውስጥ ሊካተት ይችላል ወይ**?** ማየት የተሳናቸው ወይም መሐይምናን ውል አዋዋይ አካል ወይም ዳኛ ፊት ሳይቀርቡ ወደ ባንክ በሚመጡበት ወቅት ከቤተ ዘመዶቻቸው ጋር ቢመጡ ሊስተናገዱ ይገባል ወይ**?**

ተበዳሪዎቹ ባልና ሚስት በሆኑ ጊዜ ደግሞ በተለይ የብድሩ መጠን ከብር **500** በላይ ሲሆን፣ የሁለቱም ስምምነት ስለሚያስፈልግ የብድር ውሉ ላይ ሁለቱም እንዲፈርሙ ማድረግ አግባብ ነው። የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ **68(**መ**)** ይመለከተዋል። ሆኖም ያልፈረመው ተጋቢ የብድር ውሉ የፈረመው ወገን ነጋዴ መሆኑን በመቃወም በንግድ መዝገብ ካላሰፈሩ ባይፈርሙም በብድሩ የሚገደዱ ይሆናል። የዚህ ሐሳብ ዓላማ በአንድ ወገን በተጋቢዎች መካከል የሚኖረውን የመተጋገዝና የተጠያቂነት መርህ ማጠናከር ሲሆን፣ በሌላ መልኩ ነጋዴዎች የሚያደርጉትን ኢኮኖሚያዊ መስተጋብር በትንሽ በትልቁ ቀጣይነቱን ላለማደናቀፍ ነው። በተግባር እንደሚስተዋለው ግን የፍርድ ቤት ሙግትና ውጣ ውረድን ለመቀነስ በማናቸውም ሁኔታ ባልና ሚስት የብድርም ሆነ የዋስትና ውል ላይ እንዲፈርሙ ማድረግ አግባብነት አለው። ምስክሮችን በተመለከተ ሕጉ ዘርዘር ያሉ ድንጋጌዎች አሉት። በወንጀል ሕግ ምስክር ለመሆን አካለ መጠን ማድረስ የግድ

አይሆንም። ዳኛው ማስረጃ ሲመዝን ምስክሩ በዕድሜው ተፅዕኖ የተደረገበት መሆኑን ግንዛቤ ከሚወስድ በቀር አካለ መጠን ያላደረሰ ሰው የወንጀል ምስክር እንዳይሆን የሚከለክል ድንጋጌ የለም። በፍትሐ ብሔር ሕግ ክርክር ፍሬ ነገር ለማስረዳትም እንደዚሁ ነው።

በውል ላይ ምስክር ሆነው የሚፈርሙ ሰዎች ግን አካለ መጠን ያደረሱና ያልተከለከሉ እንዲሆን አስፈላጊ ነው። የሰዎቹ ዕድ ወይም ዜግነት ምስክር የመሆንን ችሎታ አያስቀርም። አንድ ውል ምስክሮች አስፈላጊ በሆነ ጊዜ እንዲመሰክሩ የሚፈለጉት ተዋዋዮቹ ውሉን ተስማምተው የፈጸሙ መሆናቸውንና የውሉ ቃል ምን እንደሆነ ለማረጋገጥ ብቻ ነው። ከተዋዋዮቹ ለአንዱ ዋስ ነኝ ብለው ገልጸው ውል የገቡ ካልሆነ በቀር ምስክሮች ተዋዋዮቹ ግዴታቸው እንዲፈጽሙ የዋስትና ኃላፊነት የለባቸውም።

በፍርዱ ላይ የቀረበ ምልከታ

በሰበር ችሎቱ በመጨረሻ ታይቶ ፍርድ ያገኘው ጉዳይ በዋናነት የሚመለከተው የብድር ውል መኖሩን ማረጋገጥ ስለሚቻልባቸው ሁኔታዎችና የማስረዳት ሸክም ማን ላይ ይወድቃል የሚሉት ነጥቦች ናቸው። በፍርድ ቤቶቹ ከሥር ጀምሮ ከመጡት የፍሬ ነገር ክርክሮች ለመገንዘብ እንደሚቻለው የሥር ከሳሽ በቃል ባደረጉት የብድር ውል መሠረት ብር **50,000** ለተጠሪ አበድረዋቸው በባንክ ሐዋላ ያስተላለፉላቸው መሆኑን የገለጹ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ያበደርኩት ገንዘብ በሐዋላ ተልኮልኛል እንጂ ብድር አልተበደርኩም፣ ሐዋላ የብድር ውልን አያስረዳም በሚል ክደዋል። ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ፍርድ ተጠሪ በሐዋላ ገንዘብ መቀበላቸውን በማመናቸውና አበድሬ ተመልሶልኛል ሲሉ ያቀረቡትንም ክርክር ባለማስረዳታቸው ዕዳውን ሊከፍሉ ይገባል ሲል ፈርዷል። ችሎቱ የሰጠው ፍርድ ገዥ ፍርድ እንደመሆኑ መጠን የበታች ፍርድ ቤቶች ትርጓሜውን የመከተል ግዴታ ስለሚኖርባቸው ፍትኃዊነቱን መሞገት ተገቢ ነው።

በመጀመሪያ መታየት ያለበት የፍርዱ መሠረት መሠረታዊ የሕግ ስህተት በተፈጸመባት የመጨረሻ ፍርድ ላይ የተሰጠ ስለመሆን አለመሆኑ ነው። ከጉዳዩ አመጣጥ ለመገንዘብ እንደሚቻለው አከራካሪ የሆነው ጭብጥ የሥር ከሳሽ በሕግ ፊት ዋጋ ባለው የብድር ውል ገንዘብ ለተጠሪ አበድረዋል ወይስ አላበደሩም ነው። ገንዘብ ማበደራቸውን ሊያስረዱ የሚገባው ደግሞ ከሳሽ ተገቢውን ማስረጃ በማቅረብ ነው። የመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሽ ገንዘብ መቀበላቸው ያለባቸውን ዕዳ ማመናቸው ነው በሚል ብድሩ መኖሩን አረጋግጫለሁ አለ። የተለየ አቋም የሰጠው የክልሉ ሰበር ችሎት ደግሞ ከሳሽ የብድር ውሉ መኖሩን ባለማረጋገጣቸው፣ ተከሳሽም የብድሩን መኖሩን በመካዳቸው ተጠሪ ዕዳው አይመለከታቸውም ሲል ፈርዷል። ከዚህ አንፃር ከተመለከትነው የፍርድ ቤቶቹ የአቋም ልዩነት የማስረጃ ምዘና ላይ መሆኑን እንገነዘባለን። ማስረጃን መቀበል፣ መመርመርና መመዘን ደግሞ የፍሬ ነገር ጉዳይ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል በሰበር ችሎታ ለመታየት የሚበቃ ፍርድ አይደለም በማለት መከራከር ይቻላል። ይሁን እንጂ የፌዴራሉ ሰበር ችሎት መሠረታዊ የሕግ ስህተት መኖሩን ሲመረምር የያዘውን ጭብጥ ፍርዱ ስለማያመለክት ጉዳዩን የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ብቻ አድርጎ መውሰድ ተገቢነት ላይኖረው ይችላል። በፍርዶቹ በመሠረታዊነት የታየው ጉዳይ ‹‹በፍትሐ ብሔር ሙግት የማስረዳት ሸክም ማን ላይ ይወድቃል?›› ለሚለው ጭብጥ እልባት ለመስጠት እንደሆነ ጸሐፊው ያምናል። የሰበር ችሎቱ ይህን ጭብጥ ከሕጉ መሠረታዊ መርህ አንፃር ሰፊ ትንተና በመስጠት ገዥ ፍርዱን ከመስጠት ይልቅ ጭብጡን በመዝለል የብድር ውል የሚረጋገጥባቸውን የማስረጃ ዓይነቶች በመተንተን ፍርድ መስጠቱ አግባብነት የለውም።

በፍርዱ በዋናነት ሊታይ ይገባው የነበረውን የማስረዳት ሸክምን ጽንሰ ሐሳብ ብንመረምር የሰበር ችሎቱ ፍርድ የተሳሳተ እንደሆነ መገንዘብ አያስቸግርም። ማስረጃን የማቅረብ ግዴታ ‹‹የማስረዳት ሸክም›› **(Burden of proof)** የሚባለው የሕግ ጽንሰ ሐሳብ ሲሆን ማስረጃ ለፍርድ ቤት ማስረጃ የማቅረብ ግዴታንና የማሳመን ሸክምን ያጠቃልላል። በዚህ ጉዳይ አከራካሪ የሆነው በዋናነት ለፍርድ ቤት ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ **(Burden of Production)** የተመለከተ ነው። አጠቃላይ መርሁ ማስረጃ ሊቀርብበት በሚያስፈልገው አንድ ፍሬ ነገር ላይ ማስረጃ ማቅረብ የሚገባው ማስረጃ ሳይቀርብ ቢቀር በክርክሩ ተሸናፊ የሚሆነው ወገን ነው። በወንጀል ጉዳይ ሲሆን ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ የሚወድቀው በከሳሽ ዓቃቤ ሕግ ላይ ነው። በፍትሐ ብሔር ሙግትም አጠቃላይ መርሁ ተፈጻሚ ይሆናል። ማስረጃ ማቅረብ የሚገባው ማን ነው የሚለውን በተመለከተ በፍትሐ ብሔር ሕጉ በየቦታው ተሰበጣጥረው የተቀመጡ ድንጋጌዎችን እናገኛለን። ለአብነት አንቀጽ **5፣196(2) 896፣** እና **2001** ላይ የተደነገገውን መመልከት ይቻላል። ከአብዛኛው በፍትሐ ብሔር ጉዳይ የማስረዳት ሸክም ያለበት **(**ማስረጃ የማቅረብ ሸክም**)** የሚወድቀው ከሳሽ ላይ ሲሆን ወደ ተከሳሽም የሚዞር ይሆናል። ተከሳሽ ክሱን አምኖ ነገር ግን ሕጋዊ መከላከያ **(Defence)** ካቀረበ፣ የማቻቻያ ጥያቄ ካቀረበ ወዘተ የማስረዳት ሸክሙ ወደ ከሳሽ ሊዞር እንደሚችል የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር **258** ያስረዳናል። አሁን ለተያዘው የብድር ውል የመኖር አለመኖር ክርክር ጉዳይ አግባብነት ያለው ድንጋጌ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር **2001** ነው። በዚህ ድንጋጌ መሠረት ‹‹አንድ ግዴታ እንዲፈጸምለት የሚጠይቅ ሰው ለግዴታው መኖር ማስረጃ ማቅረብ አለበት።›› ስለዚህ ከሳሽ የብድር ውል ከተጠሪ ጋር አለኝ በሚል የሚከራከሩ በመሆኑ የብድር

ውሉን የማስረዳት ሸክም የከሳሽ ይሆናል። በዚህ ጉዳይ ከሳሽ የብድር ውሉ የተፈጸመው በቃል ነው ሲሉ ብድሩ ለመፈጸሙ የሐዋላው ወረቀት አስረጅ ነው ሲሉ ይከራከራሉ። ከዚህ አንፃር የብድር ውል መኖሩን የማስረዳት ሸክም የሚወድቀው ከሳሽ ላይ ነው። ተከሳሽ ገንዘቡን በብድር የተቀበልኩት ሳይሆን ቀደም ሲል እኔ ያበደርኳቸውን ብደር ከሳሽ እየመለሱ ነው በሚል ስለሚከራከሩ ከሳሽ የብድር ውል አለ ሲሉ ያቀረቡት ክርክርን ክደዋል። የብድሩን መኖር በካዱበት ሁኔታ ደግሞ የማስረዳት ሸክሙ ወደተጠሪ የሚዞርበት የሕግ አግባብ የለም። ከዚህ አንፃር ሰበር ችሎቱ ከሳሽ የብድር ውሉ መኖሩን የማረጋገጥ ግዴታ እንዳለበት የሚደነግገውን የሕግ ድንጋጌ ወደ ጎን በመተው ተከሳሽን እንዲያስረዳ መጠየቃቸው ተገቢነት የለውም።

በሌላ በኩል ሊታይ የሚገባው ነጥብ ደግሞ የብድር ወሉን ለማስረዳት መቅረብ ስለሚገባው ማስረጃ ነው። ከላይ በጽንሰ ሐሳብ ትንታኔው እንደተመለከትነው ሕጉ የብድር ውልን በተመለከተ የሚያስቀምጠው የአጻጻፍ ሥርዓት **(Form)** ባለመኖሩ ለተዋዋይ ወገኖች የተተወ ነው። የብድሩ የገንዘብ መጠን ከብር **500** በላይ ከሆነ ተዋዋይ ወገኖች በጽሑፍ፣ በፍርድ ቤት በተደረገ የእምነት ቃል ወይም በመሐላ ቃል ሊያስረዱ የሚችሉበት ሁኔታ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር **7472(1)** ተደንግጓል። የሥር ከሳሽ የብድር ውል አለኝ ሲሉ የተከራከሩ በመሆኑ ከሦስቱ አማራጮች በአንዱ በመጠቀም ሊያስረዱ የሚችሉበት ሁኔታ አለ። ሰበር ችሎቱ በሰጠው ፍርድ የሥር ከሳሽ በሐዋላ ወረቀት ገንዘቡን ለተጠሪ መላካቸው የብድር ውል መኖሩን በጽሑፍ አስረድተዋል ሲሉ መደምደሚያ ላይ ደርሷል። ለመሆኑ የሐዋላ ወረቀት የብድር ውልን ለማስረዳት ብቃት አለው**?** የሚለው ሊመረመር ይገባል። በተያዘው ጉዳይ ችሎቱ በጥሞና ሊመረመረው ይገባው የነበረው አመልካች ለተጠሪ ገንዘብ የላኩበት የባንክ የሐዋላ ወረቀት የብድር ውልን ለማስረዳት በቂ ስለመሆኑ አለመሆኑ ነው። ከትርጓሜውና ከባንክ ልምድ **(**አሠራር**)** እንደምንረዳው የሐዋላ ወረቀት **/Bill of exchange/ (**በሕጉ የተለየ ትርጓሜ እንዳለው ልብ ይሏል።**)** ገንዘብ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው በባንክ አማካኝነት ለማስተላለፍ የሚረዳ ወረቀት ሲሆን ይዘቱ ላኪውን፣ ተጠቃሚውን ከነዝርዝር አድራሻቸው ከሚገልጽ በስተቀር የገንዘቡን ዓላማ አይገልጽም። ከዚህ በመነሳት የሐዋላ ወረቀት ለስጦታ ውል፣ ለብድር ውል፣ የራስን ገንዘብ ለማስተላለፍ፣ ለሽያጭ ዋጋ፣ ለሥራተኛ ወገን ዕዳ መክፈያ፣ ለቀለብ ወዘተ. መክፈሉን ሐዋላው ሳይሆን ለሐዋላው መነሻ የሆኑ ግዴታዎች ናቸው ሊያስረዱ የሚችሉት። የሰበር ሰሚ ችሎቱ ሐዋላ የብድር ውል በጽሑፍ ያስረዳል ከማለት ውጭ ይዘቱ እንዴት እንደሚያስረዳ አለመተንተኑ አንድ ስህተት ነው። በሌላ በኩል ሕጉ የብድር ውል በጽሑፍ ይረጋገጣል ሲል የጽሑፉ ይዘት ማን አበዳሪ፣ ማን ተበዳሪ፣ ምን ያህል ገንዘብ፣ በምን የአከፋፈል ሁኔታ መቼ እንደሚከፈል የሚገልጽ ጽሑፍ እንደሆነ መረዳት አያዳግትም። ከዚህ አንፃር የችሎቱ አቋም አሳማኝ አይደለም። በችሎቱ ከሰየሙት አንዱ ዳኛ ‹‹የሐዋላ ሰነዱ በመካከላቸው የብድር ግንኙነት መኖሩን የማያረጋግጥ ከመሆኑም በላይ ተከሳሽም በባንክ በኩል የተላከውን ገንዘብ መቀበላቸውን ቢያምኑም ገንዘቡን ከተከሳሹ የተቀበሉት **.....** ለተጠሪ አበድረውት ለነበረ ገንዘብ በመክፈያነት እንደተቀበሉ ገልጸው ብድሩን ክደው ተከራክረዋል፤›› በማለት አመልካች ያለባቸውን የማስረዳት ግዴታ አለመወጣታቸውን መተንተናቸው አሳማኝ ነው። የሰበር ችሎቱ ፍርድ ወዳልተፈለገም መደምደሚያ ያደርሳል። ይኸውም ሐዋላ የላከ ሁሉ ገንዘብ እያበደረ ነው በሚል የራሱ ገንዘብ የሚላክለትም፣ ለሥራተኛ ወገን ገንዘብ የሚቀበልም ባለዕዳ መሆኑ አይቀርለትም። የሐዋላ ወረቀት ከብድር ውሉ በባህርይም፣ በዓላማም የሚለያዩ ናቸው። በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር **2471** በሕጉ በግልጽ እንደተመለከተው የብድር ውል የተዋዋዮቹን የጎዕዕር ግዴታ **(Reciprocal Obligation)** የሚያሳይ ሊሆን ይገባል። አንዱ ወገን ገንዘብ ለሌላኛው የሰጠው ከወለድ ጋር ወይም ያለወለድ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ እንዲመለስለት በማሰብ ስለመሆኑ የሚቀርቡት ማስረጃዎች ሊያረጋግጡ ይገባል። በሌላ በኩል በተያዘው ጉዳይ የሥር ከሳሽ የብድር ውሉ በቃል **(**በስልክ**)** የተመሠረተ ነው በሚል የሚከራከሩ ስለሆነ የጽሑፍ ሰነዱ **(**ሐዋላው**)** የብድር ውሉን ሊያስረዳ አለመቻሉ ከመጀመሪያውም የታወቀ ነገር ነው። ከሳሽ ብድር መኖሩን ሊያስረዱ የሚቻሉባቸው አማራጮች ለፍርድ ቤት በሚሰጡት የእምነት ቃል፣ ካልሆነም በመሐላ ቃል ብቻ ነበር። ከዚህ አንፃር የሰበር ችሎቱ የብድር ውልን ለማስረዳት የሚቀርቡ ማስረጃዎች ምን ሊሆኑ ይገባል የሚለውን በተመለከተ የሰጠው ትንተና የተሳሳተ ነው።

እንደማጠቃለያ

ሰበር ችሎቱ በሕግ የተሰጠው አስገዳጅ ትርጉም የመስጠት ሥልጣን መሠረታዊ የሕግ ስህተት በተፈጸመባቸው የመጨረሻ ፍርዶች ላይ በመሆኑ ማስረጃን አንጥሮ የመወሰንን ሥልጣን ለፍርድ ቤቶች ሊተው ይገባል። በዚህ ጽሑፍ በተመለከትነው ጉዳይ የሥር ፍርድ ቤቶች ከሳሽ የብድር ውሉ መኖሩን የሚያስረዳበትን ሁኔታ ሕጉ በሚያስቀምጠው አግባብ ቢመሩት ኖሮ ፍትኃዊ ፍርድ በተገኘ ነበር። ሰበር ችሎቱ የሥር ፍርድ ቤቶች የፍትሐ ብሔር ሙግት የማስረዳት ሸክም ያለበትን ወገን በመለየት ረገድ ስህተት ፈጽመዋል ብሎ ካመነም መርሁን በስፋት በመተንተን ገዥ የሆነ ትንታኔ **(Ratio decidendi)** ሊሰጥ ይገባ ነበር። ሆኖም ተከሳሽ የብድሩን መኖር በካደበት ሁኔታ አለመበደሩን ወይም ማበደሩን እንዲያረጋግጥ መጠየቁ የሕግ ስህተት ከማረም ይልቅ ስህተት መፈጸም ነው። ሰበር ችሎቱም ከሳሽ የሐዋላ ወረቀት በማቅረብ የብድር ውል መኖሩን አረጋግጠዋል ሲል የሰጠው ትንተና ከሐዋላ ወረቀትም ሆነ ከብድር ውል መሠረታዊ ባህርይ ጋር

የማይሄድ ነው። «ሐዋላ ሌላ የብድር ውል ሌላ» ያልነውም ለዚሁ ነው። ፍርዱ ፍትኃዊ ሆኖ ገዥ እንዲሆን ችሎቱ በሌላ ጊዜ በተመሳሳይ ጭብጥ የተለየ ትርጉም ሰጥቶት ልንመለከት ይገባል። ያ እስኪሆን ግን ፍርዱ የማስረዳት ሸክም ያለበትን ተከራካሪ ወገን በመወሰንና የብድር ውሉን ለማስረዳት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን በመለየት ረገድ ፍትኃዊነት ይጎድለዋል።

ከአዘጋጁ፦ ጸሐፊው የሕግ ጠበቃና አማካሪ ሲሆኑ፣ በኢሜይል አድራሻቸው **getukow@gmail.com** ማግኘት ይቻላል።